Diploma Programme
Programme du diplôme
Programa del Diploma

# Amharic A: literature – Higher level – Paper 1
# Amharique A : littérature – Niveau supérieur – Épreuve 1
# Amhárico A: literatura – Nivel superior – Prueba 1

Wednesday 10 May 2017 (afternoon)
Mercredi 10 mai 2017 (après-midi)
Miércoles 10 de mayo de 2017 (tarde)

2 hours / 2 heures / 2 horas

### Instructions to candidates

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a literary commentary on one passage only.
- The maximum mark for this examination paper is **[20 marks]**.

### Instructions destinées aux candidats

- N’ouvrez pas cette épreuve avant d’y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire littéraire sur un seul des passages.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d’examen est de **[20 points]**.

### Instrucciones para los alumnos

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario literario sobre un solo pasaje.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es **[20 puntos]**.

2217 – 0009



© International Baccalaureate Organization 2017

International Baccalaureate
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

https://xtremepape.rs/

ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ ስነጽሁፋዊ አስተያየት ስጥ(ስጭ)።

**1.**

መስከረም ጠባ – ቅዱስ ዮሐንስ ደረሰ፤
መስቀል ተቃረበ፤ ሜዳውን ሙሉ አደይ አበባ ፈሰሰ፤
ክረምት እንደተከፋ እንደቆረጠ አንጀቱ፤
እንደሎጥ ሚስት ደርቆ እንዳይቀር
ተከናንቦ ፀሊም ፊቱን
ዞር ብሎ ሳያይ ተገዝቶ
የመጨረሻ ድምፁን አያል ነጎድጓድ አሰምቶ፤
ነጎደ ገሰገሰ፤
ከነፋሱ ጋር ነፈሰ፡፡
ፍጥረትም – የፀሐይ ብልጭታን አፋር ፈገግታ ተመልክቶ
ተኮለኮለ፡፡
ሌቱ በዕልልታ ወንዱ በሆታ አዲሱን ዓመት ተቀበለ፡፡

ታዲያ የየህ ክስተት ፊቱ
ገጥታው መንታ ነው የጊዜ ነውጥ ምልክቱ፡–

ለእኛ – እዚህ ላለነው – ክረምት አለፈ፤
የፀደይ መምጣት በወፎች መዝሙር ተለፈፈ፤
አበቦችም ነፍስ ዘርተው ከቢራቢሮ ተዳሩ፤
ቆንጆም ከጎበዝ ሠምራ
ከተፈጥሮ ጋር ተጣቅሰው እስበሳቸው ተማተሩ፤
ፍቅር አዝመራ ተቀምሳ
የክረምት ኀዘን ተረሣ —
ለእኛ፡፡

ለእነሱ — እዚያ — ክረምት አለፈ ቢባልም፤
ከፀደይ ጋራ ፊታቸው አልፈካም—
አንድም ነፍሳቸው አልረካም፡፡
ለእነሱ —
ጠቃሽ አበባ አልበቀለም፤ አስተዋሽ ንብም አልተመመም፤
ለካብትሽ-ገብሬ የቢራቢሮ ጨዋታ እንኩዋን ህልውናቸው አልታደለም፡፡
ስለዚህም ማዶ ሰማይ የሚማተር ቆንጆና ጎበዝ የለም፤
ይጠቅሱት ቀርቶ ያያቸው ፍጥረት ፊቱን ለነሱ አላዞረም፡፡
አያችሁ!
ያ ዐፋር መሰል የፀሐይ ብልጭታ
የደመና ግላጭ ፈገግታ
(ምች ብጤ ሆኖ ግርፍታ)
የሚያሾፍ ዐይነት ደረቅ ሣቅ ሆነባቸው፤
ውሎ ሲያድር ሊደነድን
ወዝ ያጣ፤
የነጣ፤
የተንኮል ብራቅ ሆኖ ሙኘባቸው፡፡
መታቸው፡፡
ጭው! ጫ! አለባቸው፡፡

https://xtremepape.rs/

የእነሱ ታዲያ—
ክረምት አስንቆ ጭንቀታቸው
ዶፊ ፈሰሰ እንባቸው፤
ታረሰ ፊታቸው፡፡
ዘር ስለጠፋም በጨው ተዘራ
መኸራቸው እንጂ ሆነ መከራ፡፡
ምንም አልበቀለም—
ይቅር አዝመራ፤ ቡቃያ እንኳዋን አልታየም፤
ወልዶ መሳም ዘርቶ መቃም
ከወፎች ቋንቋ የረቀቀ ቅዠት ከመሆን አልዘለለም፡፡
    ለእኛ —
    እዚህ ላለነው —
    ፀደይ አለን፤ አለን ሣቅና ደስታ፤
    ዓለም በምንለው በጥንቱ ትዝታ፡፡
ለእነሱ—እዚያ ላሉት—መኸር የለም፤
ብዙም ባልተረዳን በማናውቀው ዓለም
ምትሐቱ በጠፋ፡፡

ዮናስ አድማሱ፣ ጉራማይሌ፣ (2006)፡፡



https://xtremepape.rs/

**2.**

እንግዲህ ወደ ምርምራችን እንመለስ፡፡ አጤ ምኒልክ በእውነት የሸዋ ሰውና አቶ አፈ ወርቅ እንደሚሉት አዲስ ሕግጋት አውጥተዋልን? ትምህርትንስ ገልጸዋልን? እውነት አይደለም፡፡ ይህማ ቢሆን ይህን ያህል ጊዜ በሰላም እንጀራቸውን አይበሉም ነበር፡፡ ትግሬው አለቃ ተወልደ መድህን እንደሚሉት፤ «መብራት ሳይነድ አያበራም፡፡» ስለዚህ የዓለምን ታሪክ ብንመለከት አዲስ ሥርዓት የሚያወጣ ንጉሥ ሁሉ በህይወት ሳለ መከራ አይለየውም፡፡ ሕዝቡ እንደ አውራ ደመኛው ያየዋልና፡፡ ደግነቱም የሚታወቅ ከሞተ ከብዙ ዓመታት በኋላ ነው፡፡ የአዳምን ዘር ባሕሪ በጠቅላላው ብንመለከት አዲስን ነገር የሚወድ ወገን አናገኝም፡፡ ካባቶቹ የቆየውን ካልሆነ በቀር ይልቁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ያባቶቹን ልማድ ሲለውጡበት ዝም ብሎ ባልተቀበለም፤ ጢስ እንደ ገባበት ንብ በተሸበረ በተናወጠም ነበር እንጅ፡፡ ወዮለት ለዚያው ንጉሥ የዛሬውን ከደማችን ጋራ የተዋሀደውን የድንቁርና ሥርዓታችንን ሊለውጥ ለሚነሣው፤ ለኋላ ስም ያገኛል እንጅ በሥጋው አይጠቀምም፡፡

ይህን ነገር ያጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ይመሰክርልናል፡፡ ያ ቋረኛ ንጉሥ ተበጣጥሰው የነበሩትን ያበሻን መንግሥት ክፍሎች በሰላው ጐራዴው ቀጥቅጦ አዋደደ፡፡ ሕዝቡንም ከካህናትና ከሹሞች ቀምበር አርነት ሊያወጣ አገር በጄ ብሎ አወጀ፡፡ ትምሕርትንም ሊከፍት ተከራከረ፡፡ አንባቢ ሆይ፣ በዚህ ጥረቱ ምን ተጠቀመ ይመስልሃል? በመላው ሕዝብ በካህናትና በሹሞች ተመክሮ ተነሣበት፤ አሳበደውም፡፡ በመጨረሻም ለባዕድ አሳልፎ ሰጠው፡፡ በገዛ እጁም ሞተ፡፡ አእምሮ የሌለው ሕዝብና ልጅ ጠቃሚውን አይወድም፡፡ የቴዎድሮስ አሳብ ግን አልተፈጸመም እንጅ አልሞተም፡፡ አባ ታጠቅ ለራሱ ቢከፋው የማይረሳውን ስም ተክሎ ሞተ፡፡ እውነት ነው የመነኮሳት ኃይል ገና አልላላችም፤ ሹሞቹም ብርቱ ተቆጣጣሪ ገና አልወጣላቸውም፡፡ እስካሁንም ድረስ የተሾሙበትን አገር በገንዘባቸው እንደ ገዙት ርስት ያዩታል፡፡ ከሱ በሚወጣውም ግብር የታያቸውን ያደርጋሉ፤ በታቻቸውም ያለ ሹምና አሽከር ከነሱ በቀር ሌላ ጌታ አያውቅም፤ እጣም አገኘም ከቸርነታቸው ነውና፡፡ የሆነ ሁኖ የዛሬ ሹማምንት እንደ ዱሮቹ አይደሉም፡፡ መንግሥት በላያቸው እንዳለ ጥቂት ይታወቃቸው ጀምረዋልና፡፡ እያደረም አጥብቆ ሳይታወቃቸው አይቀርም፡፡ ስለዚህ የቴዎድሮስ መንግሥት አልሞተም፤ እያደረ ሕይወት ይጨምራል እንጅ፡፡

አዲስ አበባ የኒቨርስቲ ፕሬስ፣ *ነጋድራስ ገብረ ህይወት ባይከዳኝ ስራዎች፣* (2007)፡፡

https://xtremepape.rs/